የባህልና ቱሪዝም
ሚኒስቴር

# ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ስብስቦች የአወጋገድ መመሪያ

ቁጥር 474/2013

ጥቅምት 2006 ዓ.ም.

<u>አዲስ አበባ</u>

## ቁጥር 474/2013

## የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር

## ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት

## ያጡትን ስብስቦች የአወጋገድ መመሪያ

በስብስብ ማእከል ውስጥ አንድ አይነት ቅርስ ከሚፈለገው ቁጥር በላይ ከሆነ ወይም ድግግሞሽ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም በትክክለኛ ቦታው ያልተቀመጠ ከሆነ ወደ ሚመለከታቸው ተቋማት በመስጠት ወይም በመለዋወጥ ከስብስብ ክፍሉ ማስወጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጉዳታቸው ምክንያት መጠገን የማይችሉትን ፣በመበላሸታቸው የቅርስነት እሴታቸውን በማጣት ለሌሎች ቅርሶችና ሰዎች ደህንነት አደገኛ መሆናቸው ሲረጋገጥ አንድን ቅርስ ወይም ስብስቦችን ከቅርስ ስብስብ ማዕከል በቋሚነት ማስወገድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቅርስን ከስብስብ ማዛወርና ማስወገድ በተጠና ስርዓትና ግልፅነት ባለው አሰራር መከናወን ያለበት በመሆኑ፤

በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ይህን መመሪያ አወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጡትን ስብስቦች የአወጋገድ መመሪያ ቁጥር 474/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ ካልተሰጠው በስተቀር በአዋጅ ቁጥር 209/1992 አንቀፅ 3 የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ቅርስን ከስብስብ ማእከል ማዛወር"** ማለት እንደየስብስብ ማእከሉ ከሚፈልገው ቁጥር ዓይነት በላይ የሆኑትን ቅርሶች እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሌላ ተመሳሳይ ማእከል ወይም የትምህርት ተቋማት በቋሚነት ማዛዋወር ወይም መስጠት ነው፡፡
2. **"የቅርስነት እሴት ያጣን ቅርስ ማስወገድ"** ማለት በመጎዳቱ ምክንያት ተጠግኖ ወደ ቀድሞ ይዞታው መመለስ የማይችል የቅርስነት እሴት ያጣን ቅርስ በመለየት ማስወገድ ማለት ነው፡፡
3. **"የስብስብ ማእከል"** ማለት የተለያዩ ቅርሶች ተሰባስበው የሚጠበቁበት ፣ እንክብካቤ የሚደረግበት ፣ የሚደራጁበትና ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ዝግጁ የሚሆኑበት ክፍል ወይም ማዕከል ነው፡፡
4. **"የውጭ ባለሙያ"** ማለት ቅርስን ከስብስብ በማውጣትና በማስወገድ ሂደት አስፈላጊ ሲሆን ሙያዊ አስተያየትና የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ በቅርስ አስተዳደርና አጠባበቅ እውቀት ያለው ባለሙያ ነው፡፡
5. **"ሚኒስቴር"** ማለት የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ነው፣
6. **"ባለስልጣን"** ማለት የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፤
7. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
8. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ ቅርሶች ከአንድ የቅርስ ስብስብ ማዕከል ወደ ሌላ የቅርስ ስብስብ ማዕከል የሚዛወሩበትን እንዲሁም የቅርስነት እሴት ያጡ ስብስቦች የሚወገዱበትን ስርዓት መፍጠር ነው፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት ቅርሶችን በተለያየ መንገድ አሰባስበው በሚገኙ በሀገሪቱ የተለያዩ የቅርስ ስብስብ ማዕከሎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ቅርስን ስለማዛወርና

## ስለማስወገድ 5. ቅርስን ከስብስብ ማእከል ስለማዛወር

1. በስብስብ ማእከሉ ከሚፈልገው ቁጥር በላይ የሆኑት ቅርሶች እንደ አስፈላጊነቱ ወደ ሌላ ተመሳሳይ ማእከሎች ወይም የትምህርት ተቋማት ሊዛወሩ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተጠቀሱት ቅርሶች የሚዛወሩት፡-

   ሀ. አትራፊ ላልሆኑ የምርምር ወይም ትምህርት ተቋማት ወይም ድርጅቶች ወይም ሙዚየሞች በስጦታ ወይም በለውጥ በማስተላለፍ፣

   ለ. ቅርሱን ወደ ቀድሞ ባለይዞታው በመመለስ

   ይሆናል፡፡

## 6. ቅርስ ከስብስብ ማእከል ስለሚዛወርበት መስፈርት

ቅርስ ከስብስብ ማእከል የሚዛወረው፡-

1. በስብስብ ማእከሉ ውስጥ ተመሳሳይ ቅርሶች በመኖራቸው ትርፍ ወይም ድግግሞሽ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. የቅርስ ባለይዞታዎች ቅርስን በባለቤትነት ከያዙ፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና የምርምር ተቋማት ቅርሶችን መለዋወጥ አስፈላጊነቱ ሲረጋገጥ፡፡
3. ቅርሶቹ በስጦታ ወይም በለውጥ የሚተላለፉለት ተቋም ወይም ድርጅት ለቅርሶቹ ተገቢውን ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ የሚችል መሆኑ ሲረጋገጥ

ነው፡፡

## 7. የቅርስነት እሴት ያጣ ስብስብ አወጋገድ

1. የቅርስነት እሴት ያጣ ስብስብ የሚወገደው በመጎዳቱ ምክንያት ተጠግኖ ወደ ቀድሞ ይዘቱ መመለስ የማይችል ወይም መረጃው ሙሉ በሙሉ የጠፋ ወይም ከጥቅም ውጪ ሲሆን ነው ፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና በአንቀፅ 8 በተጠቀሰው መሰረት እንዲወገድ የተመረጠው ቅርስ ከመወገዱ በፊት የስብስብ ማዕከሉ የሚወገድ የቅርስነት እሴት

የሌለውን ስብስብ ዝርዝር ለህዝብ ግልፅ በሆነ ቦታ ላይ በማስታወቂያ ይለጥፋል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት እንዲወገድ የተመረጠ ስብስብ ቅሬታ ከቀረበበት የውሣኔ ሰጪ ኮሚቴው ጉዳዩ እንደገና እንዲመረመር ያደርጋል፡፡
4. የቅርስነት እሴት የሌለው ስብስብ አካባቢን በማይበክል ሁኔታ በማቃጠል ወይም በመቅበር እንዲወገድ ይደረጋል፡፡
5. የቅርስነት እሴት የሌለው ስብስብ ሲወገድ የፖሊስ እና የመገናኛ ብዙሃን ተወካዮች ተገኝተው ሂደቱን እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡

## 8. የቅርስነት እሴት ያጣ ስብስብ ስለሚወገድበት መስፈርት

የቅርስነት እሴት ያጣ ስብስብ የሚወገደው

1. በስብስብ ውስጥ ያለ ቅርስ በመጎዳቱ ወይም ተሰብሮ አካሉ በመጉደሉ ሊጠገን የማይችልና የቅርስነት እሴት ያጣ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ቅርሱ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋ ምክንያት በመጎዳቱ ወይም በመበላሸቱ ምክንያት የቅርስነት እሴት ያጣ እና ለሌሎች ቅርሶችና ለሰዎች ደህንነት አደገኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፣
3. በሚደረግ ጥናት የቅርስነት እሴት እንደሌለው

ሲረጋገጥ ነው፡፡

## ክፍል ሶስት

## ኮሚቴ

## ስለማቋቋም

## 9. የቴክኒክ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. ቅርስን ከስብስብ ለማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጣን ስብስብ ለማስወገድ አጥንቶ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የቴክኒክ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. የስብስብ ማዕከሉ ሃላፊ------------------------------------ ሰብሳቢ
2. አግባብ ያለው ባለሙያ----------------------------------- አባል
3. የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ባለሙያ ----------------------- አባል
4. የቅርስ እንክብካቤና ጥገና ባለሙያ----------------------- አባል

5. የቅርስ ዶክመንቴሽን ባለሙያ -------------------------------- አባልና ፀሐፊ

## 10. የቴክኒክ ኮሚቴው ስብሰባ

1. ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፡፡ ድምፁ ለሁለት እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡
4. ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 11. የቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

1. በስብስብ ማዕከሉ ኃላፊ ቅርስ ከስብስብ እንዲዛወር ወይም የቅርስነት እሴት ያጣ ስብስብ እንዲወገድ ሃሳብ ሲቀርብለት በመስፈርቶቹ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግ ጣል፡፡
2. ቅርስ ከስብስብ እንዲዛወር ወይም የቅርስነት እሴት ያጣ ስብስብ እንዲወገድ የቀረበው ጥያቄ መስፈርቶቹን ያላሟላ ከሆነ ከባለሙያዎቹ ጋር በመወያየት ቅርሶቹ በአግባft እንዲያft ያደርጋል፡፡
3. በቅርስ አጠባበቅ ባለሙያ በማስመርመር የቅርስነት እሴት ያጡ ቅርሶች የሚወገዱበትን የተሻለ መንገድ ያመቻቻል፡፡
4. የስብስብ ማዕከሉን አላማና የቅርስ አሰባሰብ እቅድ ወይም ሌሎች ክልላዊና አካባቢያዊ ህጎች ባገናዘበ መልኩ የቅርስነት እሴቱን ያጣ ስብስብ የሚወገድበትን ምክንያት የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ከስብስft ክፍሉ እንዲቀርብ ያደርጋል፡፡
5. ከስብስብ የሚዛወር ቅርስ ወይም የሚወገድ የቅርስነት እሴት ያጣን ስብስብ የሚመለከቱ ውሳኔዎችን የያft የፎቶግራፍና ሌሎች መረጃዎች ጭምር በተሟላ ሁኔታ በስብስብ ክፍሉና በዶክመንቴሽን ክፍሉ መያዝና ለወደፊቱም የሚጠበቁበትና የሚተላለፉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡
6. ቅርሱን የሰጠው ወገን ያስቀመጣቸው ገደቦች ካሉ የቅርሱን ማህደር በማየት ያረጋግጣል ፡፡
7. ቅርስ ከስብስብ እንዲወጣ ወይም የቅርስነት እሴት ያጣው ስብስብ እንዲወገድ የተሰጠውን የውሳኔ ሀሳብ ለመጨረሻው ውሳኔ አፅዳቂ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

8. የሚመለከታቸው አካላት ቅርሱ ከስብስብ የሚዛወርበትን ወይም የቅርስነት እሴት ያጡ ስብስቦች የሚወገዱበትን ምክንያት በመገናኛ ብftሃን እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡
9. በአምስት አመታት ውስጥ ከስብስብ የተዛወሩ ወይም የተወገዱ የቅርስነት እሴት ያጡ ስብስቦችን ዝርዝር የያዘ ሰነድ ተዘጋጅቶ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል እንዲሰራጭ ያደረጋል፡፡

## 12. የውሣኔ ሰጪ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1. ከቴክኒክ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ቅርስን ከስብስብ የማዛወርና የቅርስነት እሴት ያጣን ስብስብ የማስወገድ ውሳኔ ተመልክቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥ ውሣኔ ሰጪ ኮሚቴ ይቋቋማል፡፡
2. የውሣኔ ሰጪ ኮሚቴ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ፤
   1. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ----------------------------------------ሰብሳቢ
   2. ከሚመለከተው የሀይማኖት ተቋም ተወካይ--------------------------አባል
   3. የቅርሱ ባለይዞታ------------------------------------------------------አባል
   4. የቅርስ ባለድርሻ አካላት ተወካይ--------------------------------------አባል
   5. የቅርስ ቁጥጥርና ክትትል ሃላፊ--------------------------------------አባል
   6. ከቅርስ ጋር ተያያዥ ሙያ ያለው ከተቋሙ ውጭ ያለ ባለሙያ---አባል
   7. የስብስብ ማዕከሉ ሃላፊ ------------------------------------------------አባልና ፀሐፊ

## 13. የውሳኔ ሰጪ ኮሚቴ ስብሰባ

የውሳኔ ሰጪ ኮሚቴው ስብሰባ ሥነ-ሥርዓትና የውሳኔ አሰጣጥ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 10 መሠረት ይሆናል፡፡

## 14. የውሣኔ ሰጪ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1. ቅርስ ከስብስብ እንዲዛወር ወይም የቅርስነት እሴት ያጣው ስብስብ እንዲወገድ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ በመስፈርቱ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፤
2. በቴክኒክ ኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ በመመርመር የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. ማንኛውንም የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች በቋሚ ማህደሩ ውስጥ ተመዝግበውና ወቅታዊ ተደርገው እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ

15. **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

1.ለሳይንሳዊ ጥናትና ትንተና አስፈላጊ የሆነን የቅርስ ናሙና ሰባብሮ ወይም ፈጭቶ ማጥናት ሲያስፈልግ በዚህ መመሪያ የተቀመጠውን የማስወገድ መደበኛ አሰራር መከተል ላያስፈልግ ይችላል፡፡

2. ከስብስብ ማዕከል ከሚዛወር ቅርስ ሊገኝ የሚችል የገንዘብና የቁሳቁስ ስጦታ በመንግስት የፋይናንስ ስርዓት መሠረት በህጋዊ መንገድ ለሚመለከተው አካል ገቢ ይደረጋል፡፡

16. **ክልከላ**

ምትክ የሌላቸው ናሙናዎች፤ በመጥፋት ላይ ያሉ ዝርያዎች፤ የአርኪዎሎጂና ፓሊዮንቶሎጂ ግኝቶች ወይም ቅሪቶች፣ የአሐዝና የምስል ናሙናዎች፣ በማንኛውም ሳይንሳዊና ሙያዊ ህትመቶች ላይ የወጡ ናሙናዎች አይወገዱም፡፡

17. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ ስራ ላይ በማዋል ረገድ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

18. **ቅጣት**

ይህን መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

19. **ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ህጎች**

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በመመሪያው በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

20. **መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውሊያሻሽለው ይችላል፡፡

21. **መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ጥቅምት 13 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡